የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21[th] Year No. 46
ADDIS ABABA, 25[th] May, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፫/፪ሺ፯ ዓ.ም

ለመሠረታዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ምዕራፍ ፫ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ..........ገጽ ፰ሺ፪፻፵፯

**CONTENTS**

Proclamation No. 893/2015

Government of the Italian Republic Loan Agreement for Partially financing Promoting Basic Services Program-Phase III Project Ratification Proclamation..................................page 8247

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፫/፪ሺ፯ ዓ.ም

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው ብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመሠረታዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ምዕራፍ ፫ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈፀሚያ የሚውል ፰ ሚሊዮን ዩሮ (ስምንት ሚሊዮን ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል እ.አ.አ ሴፕቴምበር ፭ ቀን ፪ሺ፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፳፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 893/2015

## A PROCLAMATION TO RATIFAY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE ITALIAN REPUBLIC

WHEREAS, the Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic provides to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan in an amount of Euro 8,000,000 (Eight million Euro) for partially financing Promoting Basic Services program – Phase III Project was signed in Addis Ababa on the 5[th] day of September 2014;

WHEREAS, the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 30[th] day of April ,2015;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is here by proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ Unit Price 6.45

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለመሠረታዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ምዕራፍ ፫ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፫/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል እ.አ.አ ሴፕቴምበር ፭ ቀን ፪ሺ፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመ የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፰ ሚሊዮን ዩሮ (ስምንት ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የማፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as the "Government of the Italian Republic Loan Agreement for Partially financing Promoting Basic Services Program-Phase III Project Ratification Proclamation No. 893/2015".

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement signed in Addis Ababa on the 5th day of September 2014 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 8,000,000 Euro (Eight Million Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa this 25th day of May, 2015**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት